# የሐምሌ 6 1997 ዓም ( ጁላይ 13 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሰ ሐተታ

## ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር በመራጭ ድምፁ ለመለስ አገዛዝ ወግድንና ሽንፈትን እንዳከናነበው እየታወቀ፤ አገዛዙ ቆጠራውን አስቁሞ የማጭበርብር ድርጊቱን በጠራራ ፀሐይ ሲፈፅም መጋለጡ እየታየ ፤የምርጫ ቦርድ ተብዬው ጉድ ደግሞ የመለስ ሎሌዎች መጠራቀሚያ መሆኑ ለዓለም ሳይቀር ግልፅ ሆኖ እያለ የመለስ ቡድን የምርጫውን ውጤት ለማሳወቅና ራሱን ለአንዴም ለሁሌም አሸናፊ ብሎ ለመሰየም ቀነ ቀጠሮውን ማብዛቱ፤ ማራዘሙ እየታየ ነው:: አደብ ገዝቶ፤ራሱን ታዝቦ፤ ሀቀኛ ቆጠራን ሊያካሂድ ብሎ ሳይሆን ጊዜ እየገዛ እየተሰናዳ መሆኑ ለማንም ኢትዮጵያዊ የተደበቀ አይደለም::

ጊዜ ባገኘ ቁጥር የማጭበርበር ስራውን ያራቅቃል:: በተንኮል ተቃዋሚ ኃይሎችን ይከፋፍላል:: ማደናገሪያና ማዘናጊያ ሸሮችን ይሸርባል:: ተቃዋሚዎችን ለማሰርና ለማሳደድ ጊዜ ያገኛል:: ባዕዳንንም ከእኔ ሌላ ከመጣ ሀገርና አካባቢ ይሸበራል ብሎ ለማሳመን መፍጨርጨሪያ ጊዜ ያገኛል:: የተጭብረበረ ድሉን ሲያውጅም የሕዝብ ቁጣ ሊነሳበት እንደሚችል ከወዲሁ ይገምታልና ለዚህም ይዘጋጃል:: ከማንም ዕይታ ያልተደበቀው ሀቅ አገዛዙ ድርጅቱ በምርጫው መሸነፋቸው ነው:: ይህን ሀቅ ለመቀበል ደግሞ ለመለስ ቡድን ፅሬት ሆኖበታልና ሕዝብን በመጨፍጨፍ፤ ተቃዋሚ ኃይሎችን በማሸበርና በባዕዳን ተፅዕኖ ሽንፈትን እንዲቀበሉ በማድረገግ ሰርጎ ገቦቹን በማሰማራት ሁኔታውን ለመገልበጥና ሀሰቱን ተቀባይ አድርጎ ለማስፈን ይጥራል:: ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንዲሉ አይቀሬው ጉዳይ ግን የመልስ ቡድን ከስልጣን በሕዝብ ድምፅ መወገዱና ለአንድ ቀንም ከአሁን ወዲያ ቢቆይ ያው በህገወጥነቱ መሆኑ ነው:: ባዕዳንም ይህንን ጠንቅቀው ያውቁታል:: ግን እነሱ ሀቅን በኢትዮጵያ ለማስፈን ሊሟሟቱ አይጠበቅባቸውም:: ጥቅማቸውን ያስቀድማሉና መለስ ዜናዊ ቡችላቸው ሆኖ እስከቆየ ድረስ ዕድሜ ሊሰጡት ይፈልጋሉ:: ለዚህም ነው በተቃዋሚ ኃይሎች ላይ አለአግባብ ተፅዕኖ ሲያደርጉ የቆዩት:: ለዚህም ነው በሌሎች ሀገሮች እንዳደረጉት ሁሉ ሕዝብ ወግድ ብሎሀልና ተነስ ቦታ ልቀቅ ብለው ጫና የማያደርጉበት:: ሊያድኑት የሚፈልጉት ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የቆመ ሆኖ ስለቆየ ስላስመሰከረም ነው:: ከዚያ ባሻገር ደግሞ ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ቦታና ሚዛ በአፍሪካ ቀላል ባይሆንም አህጉሩ በአጠቃላይ ደግሞ በኃያላኖቹ የሚሰጠው ሚዛ ከባድ አለመሆኑ መታወቅ ያለበት ነው::

ተዓምር ካልተከሰተ በስተቀር የምርጫ ቦርዱ ከሶስት ሳምንት በኋላም ሆነ ከሶስት ወር በኋላ የሚያውጀው ቢኖር ያው ኢሕአዴግ ምርጫውን አሸንፏል የሚል ነው:: ባዕዳኑም ይህን ተቀብላችሁ መለስ ዜናዊ በሚቆጣጠረው ፓርላማ ግቡና አምስት ዓመት ጠብቁ ማለታቸው አይቀሬ ነው:: ከተቃዋሚ ኃይሎች ውስጥም ቢሆን አንዳንዶቹ ጎመን በጤና፤ያገኘነውን ወንበር ይዘን ጠባይ አሳምረን እንገዛ ማለታቸው የሚጠበቅ ነው:: የሕዝብን ድምፅ አናስደፍርም፤አናሰርቅም ብለው ፀንተው የሚቆሙና የሕዝብን ከበሬታ የሚያተርፉ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች መኖራቸው ደግሞ የሚጠበቅ ነው:: ወደ ፖለቲካው መድረክ ሁሉን ባስደነቀ ቆራጥነት የገባውና መስዋዕትነት የከፈለው ሕዝብ ደግሞ የመለስን ቡድን ማጭበርበር ላለመቀበል ቆርጧል:: የመለስ ቡድን ደግሞ ከ "በልዎ"፤ግደል-ጨፍጭፍ፤ ጨቁን ዛሩ ገና ያልተላቀቀ ስለሆነ አግአዚም ሌላም እያለ ነፍስ ገዳዮችን አሰማርቶና አረመኔያዊ ሽብርን አካሂዶ በስልጣን ሊቆይ አቅዷል:: የኃይሎች አሰላለፍ እምብዛም ምስጢር አይደለም:: ሰላማዊ ትግል ሲሉ ቆይተው ዛሬ የሕዝብ አመፅ የሚለው ቃሉም ለምን ተሰምቶ የሚሉት ሰልፋቸው ከማን መሆኑ ግልፅ ሆኗል:: የተቃዋሚ ኃይሎችን ህብረት በሰበብ አስባቡ የሚያፋልሱትም በአደባባይ እርቃናቸውን ወጥተዋል:: በአጭሩ ማን

ማን እንደሆነና የት እንደቆመ ግልፅ ነው ማለት ይቻላል። ይህ ደግሞ ለትግሉ ጠቃሚ ክስተት ነው።

የት ደርሰናል የሚለው እምብዛም ግራ የሚያጋባ ባይሆንም ምን መደረግ አለበት የሚለው ላይ ግን የሰመረ አስተሳሰብና አመለካከት አለ ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር የሚቻል አልሆነም። ይህ ግን ወሳኝ ጉዳይ ነው። ተቃዋሚ ኃይሎች በተቀናጀ መልክ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል። ሕዝብ ድርጅታዊ መተሳሰርና መቀናጀትን ይፈልጋል። ድርጅቶች ራሳቸውን በራሳቸው የሕዝብ መሪ ብሎ መሰየምን ትተው በተጨባጭ በትግልና በድርጊት-በተግባር ትግሉን ሲያራምዱና ሲያጠናክሩ መታየት ይኖርባቸዋል። ደግምን ደጋግመን ለማሳሰብ እንደሞከርነው ካለፈው ተመክሮ መማር መቻል አለብን። በደም ዋጋ የተገኘ ትምህርትና ተመክሮ ነውና ከደጉም ከስህተቱም ትምህርት መቅሰም ይገባናል። ግራ ቀኙን ስንቃኝ ዛሬ የመለስ ቡድን የሚፈልገውን አውቆና ዕቅዱን አውጥቶ ሲንቀሳቀስ የተቃዋሚው ጎራ ግን ይህን እያደረገ አይደለም። ለጠላትም ዝግ ነው ማለት አይቻልም። በየቦታው በደልና ግፍ የበዛበት ሕዝብ ለመራራው ትግል እየተዘጋጀና እርምጃ እየወሰደም ነው። ፈረንጆች ይህን ብለዋልና ብሎ ለመለስ ቡድን አስከፊ በቀል ራሱን-አንገቱን ሊሰጥ ፍላጎት የለውም። አመፅ ተብሏልና በተባለው መሰረት በሰላም አምጿል። ብረት አታንሳ ሲሉት ከርመው ዛሬ ባለማዊ ሕዝባዊ አመፅ ሲሰመራ ደግሞ አናውቅህም ወይም አመፅ ሲባል ቃሉ ራሱ የማናል የሚሉ ብቅ ካሉ ይህ ግራ ቢያጋባው ሲያንስ ነው። ሰላማዊ ሕዝባዊ አመፅ ህገ ወጥና ወንጀል ከሆነና ከተባለ መውጫ ፈላጊው ሕዝብ ወደ ብረት ማንሳቱ ቢሸጋገር ጥፋቱና ተጠያቂነቱ የመለስ አገዛዝ እንጂ የሌሎች ሊሆን አይችልም። ጭቆናን ተቀብለህ ቀጥል ብሎ መካሪ ተቃዋሚ ነኝ ካለ ቧልት ነው። ባዕዳን ቢሉ ይገባናል፤ በጫንቃችን ያለው ሸክም አይከብዳቸውምና።

የመለስ አገዛዝ መሰረቱ ሕዝብን እርስ በርሱ ማጋጨት ነውና ይህ ዘረኛ ፖለቲካውን ዛሬ በዋናነት ይዞ እየገፋበት ነው። የትግራይ ሕዝብ ላይ መርገምና ዕልቂት የመጣ አስመስሎ በማቅረብ ይህን ሕዝብ ከቀሪው ኢትዮጵያዊ ሊያዳግ እየጣረ ነው። የትግራይ ተወላጆች ከሕዝቡ የተቃውሞ ትግል ጋር እንዳያብሩ በሁሉም መስክ እየቀሰቀሰ ነው። በተወሰነ ደረጃ ይህ ጥረቱ እንደተሰካላት ደግሞ መካድ አይቻልም። በሀገር ቤትም ሆነ ባዕድ ሀገሮች ብዙዎቹ የትግራይ ተወላጆች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በፀረ መለስ አገዛዙ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ሲሳተፉ አልታዩም። ይህ አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን አሳሳቢም ነው። ተቃዋሚዎችን የአንድ ብሄረሰብ ተወካዮች አድርጎ በመፈረጅና በፀረ ትግሬነትም በመክሰስ አገዛዙ የትግራይ ተወላጆች በስጋት እንዲዋጡ እያደረገ ነው። የትግራይ ምሁራንና ተቃዋሚ ነን የሚሉት ቡድኖች ከመቸውም በበለጠ ስራ ይጠብቃቸዋል። ተቃዋሚ ድርጅቶቸ በኡቃላይም ይህንን የአገዛዙ ከፋፋይ ቅስቀሳ ለማክሸፍ መጣር አለባቸው። ሕዝብ በትግሉ እውን ሊያደርግ የሚፈልገው የሁሉም ዜጋ ሀገር የሆነች ኢትዮጵያን እንጂ የቢ.ሄረሰብ ወይም የህይማኖት ጭቆና የሰፈነባትን ወይም ወያኔያው ዘረኝነት የነገሰባትን ኢትዮጵያን አይደለምና ይህም በግልፅ መነገር አለበት። የትግራይ ተወላጆች የነገ ዕጣቸው ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋር የተቆራኘ ሊመስላቸው አይችልም።

ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ስንል ደግሞ አገዛዙ በተመለከት ሊኖር የሚችለውንም ብዥታ ይመለከታል። የመለስ ቡድን ከናቅፋ ደደቢተ ወስዶ ለጥፋት ጉዞውና ለዛሬ ያደረሰው ሰይጣን እያቀሰሰው ነው። የተለወጠው ነገር የለም፤የተሻሻለ ገፅታና ድርጊት ከቶም ሊኖረው የሚችል ቡድን አይደለም። ፀረ ኢትዮጵያነቱ ደግሞ መለያው ነው፤ ፀረ ህዝብነቱ ማንነቱን ገላጭ ነው። የመለስ ዕብሪትና ቅጥፈት፤ የቡድኑ ሰው በላነት አየለ ጨመረ እንጂ አልቀነሰም። ለዚህም ነው ከዚህ መሰሪና ፀረ ሕዝብ ቡድን ጋር መፈራረም ገና ከመጀመሪያው ፍሬ ቢስ የነበረው። ዛሬ እየታየ እንዳለው ደግሞ የፈረመውን እንኳን

የማያከበር ነው። አፈናውን ቀጠለበት እንጂ አላቆመውም። የምርጫ ቦርዱን ተጠቅሞ ማጭበርበሩን ቀጠለ እንጂ ሽፍጡን አልተወም። በምናውቀው ወያኔነት ገሰገሰ እንጂ የሕዝብን ተግሳፅ አላደመጠም። ይህ ከበፊቱም የሚታወቅ ነውና በዚህ ላይ ዳግም ውዝግብር መስፈኑ ለተመልካች የሚገባ ጉዳይ አልሆነም። ተቃዋሚ ኃይሎች አንድነታቸውን ፈርጠም አድርገው ይዘው፤ የባዕዱን አግባብ የለሽ ተፅዕኖ አንቀበልም ብለው፤ ከመለስ አገዛዝ ጋር በማይፈይድ ፉርማና ስምምነት ውስጥ መግባት አልነበረባቸውም፤አሁንም የለባቸውም። የምርጫ ቦርዱን ውሳኔ እንቀበላለን፤እናከብራለን ብሎ መፈረም ለትግሉ ጎጂ መሆኑ ሳይተላም የተፈታ ነውና ከዚህ አጣብቂቅ/ በጊዜ መውጣት መቻሉ የግድ ይሆናል።

ደግመን ደጋግመን እንዳልነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአንዴም ለሁሌም ከዚህ አረመኔና ሀገር አጥፊ አገዛዝ ለመገላገል ይፈልጋል እንጂ እንቶኔና እንቶኔ የፓርላማ አባል ወይም ከንቲባ እንዲሆኑ ሲል ደሙን አልገበረም። መስዋዕትነት ከፍሎ ያደሰው ታሪክ ደግሞ ለሀገርና ለሕዝብ ታግሉ፤ለጨቋኝና ለባዕድ አትንበርከኩ የሚል እንጂ የአገዛዙ ወዳጅ የሆኑ ባዕዳንን ምክርና ተፅዕኖ ተቀበሉ የሚል አይደለም። ይህ ግልፀ መሆን አለበት። ድርጅቶች የሕዝብ ትግል መሳሪያ እስከሆኑ ድረስ ነው ጥቅማቸው። ሁሉን አዋቂና ወሳኝ ድርጅት ወይም መሪ ሊኖር አይችልም። ሕዝብም የራሱንና የሀገሩን ዕጣ ለድርጅቶች ወይም ለመሪዎች አሳልፎ መስጠት የለበትም። ጨቋኝ በጨቋኝ እየተተካ ዕዳችን ፍዳችን አላቆም ያለው ድላችንን ሁሌም ስለምንነጠቅ ነው። በየካቲት ወቅት ደርግ የገባለ ጉድ የሕዝብን ትግል ሊቀማ ሲነሳ ተጠንቀቅ የሀገር ልጅ፤ታገል፤ ሞግዚት አትሻ ብሎ ኢሕአፓ የትግል ጥሪ ሲያስተጋባ ኢትዮጵያ ትቅደም አለምንም ደም፤ ደርግ ነፃ ሊያወጣን ነው እያሉ የታለሉና አልፎም ከዚሁ ደርግ ጋር ያበሩ እንደነበሩ እናስታውሳለን። ዛሬም ሕዝብ ከዚሁ በመማር ማን ለጥቅሙ እየታገለ አንደሆነ፤እነማን ደግሞ ለረሳቸው ጥቅምና ለውሱን ድርጅታዊ ዕቅድ እየታገሉ እንደሆኑ መለየት መቻል አለበት። ባፈተታችሁ ምሩን፤ ካሰኛችሁ ገደል ጨምሩን፤ ከፈለጋችሁ ከመለስ ዜናዊ ጋር ተስማምታችሁ ፓርላማ ገብታችሁ ስንመተር እዩን ብሎ ፈቃድ ሕዝብ ለማንም ሊሰጥ መጠበቅ የለበትም። ሕዝብን ተክቶ መቆምና በሕዝብ ስም መወሰን መናገር አምባገነንነትን ማቀንቀን ነው። በተመክሮ ወደ ተውነው ግንባር ቀደም ፓርቲ ፈሊጥ መመለስም ይሆናል።

የድርጅቶች ህብረት ለትግሉ ድል ወሳኝ መሆኑን ሳይነገር የቀረ ጉዳይ ባይሆንም ዛሬ ባለንበት ወሳኝ ወቅት የተቃዋሚዎች መተባበር ቁለፍ ጥያቄ ሆኖ ይገኛል። የተቃዋሚ ኃይሎች መተባባር አለመቻል ለሕዝብ ጠላት እንደሚያመች የላፈው ተመክሮአችን አሳይቷል። የብቻ ሩጫ ለሽልማት ሳይሆን ለውድቀት ዳራጊ ነው። ድርጅታዊ ትምክህት ደግሞ በቁርጥ ቀን ፈተና ፀሐይ የመታው ጤዛ ሊሆን ይችላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለተቃዋሚዎች ድጋፍ የሰጠው አገዛዙ ስለጠላና ማስወገድ ስለፈለገም ነው። ይህ ግብ እንዲደርስ ደግሞ ተቃዋሚዎች ተባብረው እንዲታገሉ ይፈልጋል። ይህ እንዳይሆን የሚያግዱት ደግሞ የትግሉ ጠር እንጂ ወዳጆች ሊባሉ አይችልም። ሕዝብም ሊያጋልጣቸውና ሊያወግዛቸው ያስፈልጋል። የአገዛዙ ሰርጎ ገቦች በተቃዋሚዎች መሀል ክፍፍልን በስልት እየነዙ ነው። አንዱን ደጋፊ መስለው ሌላውን ያወግዛሉ። አንዱን እያጠቁ ሌላውን--እንዲጠረጠር--በዝምታ ያልፉታል። ሌሎች ዘዴዎችንም በመጠቀም ሁሌም ክፍፍልና ንትርክን ያናፍሳሉ። ድርጅቱ ተሰንጥቋል ብለው ያደናግራሉ፤ በዋልታ፤በራዲዮ ፋናና መሰል መገናኛዎች እያሰራጩ ያሉት ለዚህ ምስክር ነው። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ አላዋቂ ሳሚዎች በርክተዋል። ወደ ፖለቲካው ዓለም አለምንም ዝግጅትና ግንዛቤ ዘው ብለው ገብተውና አንዱን ወይ ሌላውን ድርጅት በጭፍኑ አቅፈው ከድርጅቱ ሌላ ለአፈር ብለው ይረብሻሉ። ሳይወዱና ሳያወቁ --ሳይገባቸውም ማለት ይቻላል-- ለመለስ አገዛዝ ይጠቅማሉ። ይህን ሁሉም ማስቆም ያስፈልጋል። ተቃዋሚ ኃይሎች ልዩነቶቻቸውን አርግበው በዋናው ግብ ላይ ማተኮር አለባቸው። ይህም የመለስን አገዛዝ ወደ ታሪክ ትቢያ መጣል ነው። ይህ ግብ ከተሟላ በኋላ በፕሮግራም ልዩነት ነጥቦችና ምርጫዎች ላይ የመነታረኩ ዕድልና ጊዜ ሊኖረን ይችላልና ነው።

የሀገራችን ሰው ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ብሏል፡፡ ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት እንዳይባልብንም መጠንቀቅ አለብን፡፡ ከ 14 ዓመት አሰቃቂ አገዛዝ በኋላ ዛሬ ስለ ወያኔ ወይም መለስ የምንደናገርበት ነጥብ ሊኖር አይችልም፡፡ ለመለስ ዜናዊ መጎንበስን ከመረጥን ግን ይህ ሁሉ ጉንጭ አልፋ ነው፡፡ ፀጥ ለጥ ብሎ ለመገዛት ብዙም ሽር ጉድ አይጠይቅም፡፡ሕዝብ ግን ውሳኔና ምርጫው ሌላ ነውና በመለስ ቡድን ከእንግዲህ ሊደናገር አይፈልግም፡፡ ጊዜ አልፏል፣አብቅቷል፡፡ የሚፈልገው የአገዛዙ  ውድቀት ነው፡፡ ይህን ፍላጎቱን አሟልተው ትግሉን ከግብ ለማድረስ ደግሞ የተቃዋሚ ኃይሎች ተባብረው መጣር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከታሪክ ትዝብት ለማምለጥ፣ሀገርን ለማዳን፣ ሰብዕናንም ለማስከበር፡፡ለባዕዳኑም እምቢ ካልገባቸው ሕዝቡ በላቡ አስተምሮናልና ኖ፣ኔቨር እንበላቸው፡፡

ነገ የሚሆነው ዛሬ ግልፅ ነውና ለወሳኙ ፍልሚያ እንዘጋጅ፡ እንደራጅ፡፡